**የታቀደ የክፍል እርምጃ ስምምነትን በተመለከተ ማስታወቂያ**

**GARNETT V. ZEILINGER**

**የሚከተለውን ካደረጉ ይህንን ማስታወቂያ ማንበብ አለብዎት፦**

- **በጁን 1፣ 2016 እና ኦገስት 24፣ 2023 መካከል የSNAP ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ማመልከቻ ወይም ዳግም ማረጋገጫ ማመልከቻ ለዲሲ ዲፓርትመንት ኦፍ ሂዩማን ሰርቪስስ ካስገቡ እና በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልደረስዎት፣ ወይም**

- **በጁን 1፣ 2016 እና ኦገስት 24፣ 2023 መካከል የSNAP ጥቅማጥሞችን በDHS ዳግም ለማረጋገጥ ከነበረብዎት፣ እንዲያረጋግጡ ከDHS ተገቢው ማስታወቂያ ካልደረስዎት እና ጥቅማጥቅሞችዎ ከተቋረጠ።**

በፌደራል ፍርድ ቤት ሙግት ያለ ስምምነት፣ *Garnett v. Zeilinger* ፣ ህጋዊ መብቶችዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያደርግ ይችላል። በ*Garnett* ያሉ ከሳሾች የዲሲ ዲፓርትመንት ኦፍ ሂዩማን ሰርቪስስ ተጨማሪ የምግብ እርዳታ ፕሮግራም (ሳፕሊመንታል ኑትሪሽን አሲስታንስ ፕሮግራም) (ስናፕ) ማመልከቻዎችን በሰዐቱ ማስኬድ አለመቻሉን እና DHS ጥቅማጥቅሞቻቸውን እንደገና ማረጋገጥ ለሚያስፈልጋቸው የSNAP ተቀባዮች በህጋዊ መንገድ የተጠየቁ ማስታወቂያዎችን አልሰጠም። ተዋዋይ ወገኖች በጉዳዩ ላይ ይፋ ስምምነት ለመስጠት ተስማምተዋል፣ ይህም በፍርድ ቤት መጽደቅ አለበት።

**የታቀደ ስምምነት**

የታቀደው ስምነት ቅጂ በhttps://dhs.dc.gov/page/proposed-snap-settlement ይገኛል። ስለታቀደው ስምምነት ጥያቄ ካለዎት፣ የህግ እርዳታን በ202-221-8222 ማነጋገር ወይም ለ snapsettlement@legalaiddc.orgኢሜይል መላክ ይችላሉ።

**ስምምነቱን የሚመለከተው ማንን ነው?** ፍርድ ቤቱ ሶስት የተለያዩ ክፍሎችን አረጋግጧል። ስምምነቱ ከክፍሎቹ በአንዱ ውስጥ ለሚገኝ ሁሉም ሰው ይሰራል። ከሚከተሉት ሶስት ምድቦች ውስጥ በአንዱ የሚስማሙ ከሆነ የክፍል አባል ነዎት፦

a. ከጁን 1፣ 2016 ጀምሮ ሁሉም የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪዎች፡- (1) በመነሻ ማመልከቻ በኩል ለSNAP ጥቅማጥቅሞች ያመለከቱ፣ እያመለከቱ ያሉ፣ ወይም የሚያመለክቱ፤ እና (2) በህግ ከተደነገገው የጊዜ ገደብ በላይ የዘገየ የዚህ አይነት ማመልከቻ ዘግይቶባቸው የነበረ ወይም የሚዘገይባቸው፤

b. ከጁን 1፣ 2016 ጀምሮ ሁሉም የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪዎች፡- (1) በእንደገና ማረጋገጫ ማመልከቻ በኩል ለ SNAP ጥቅማጥቅሞች ያመለከቱ፣ እያመለከቱ ያሉ፣ ወይም የሚያመለክቱ፤ እና (2) በህግ ከተደነገገው የጊዜ ገደብ በላይ የዘገየ የዚህ አይነት ማመልከቻ ዘግይቶባቸው የነበረ ወይም የሚዘገይባቸው፤

c. ከጁን 1፣ 2016 ጀምሮ ሁሉም የኮሎምቢያ ዲስትሪክት SNAP ተቀባዮች፡- (1) የSNAP ጥቅማ ጥቅሞችን ለመጠበቅ የእንደገና ማረጋገጫ ማመልከቻ ማቅረብ የነበረባቸው ወይም ማቅረብ የሚጠበቅባቸው፤ (2) ተከሳሹ የእንደገና ማረጋገጫ አስፈላጊነት ማስታወቂያን ሊሰጣቸው ያልቻለው ወይም ወደፊት የማይችለው ሰዎች፤ እና (3) ተከሳሹ ይህን ማስታወቂያ ባለመስጠቱ ምክንያት SNAP ውስጥ ከመሳተፍ የተሰረዙ ወይም ወደፊት የሚቋረጡ፤

እና

ለSNAP ጥቅማጥቅሞች አመልክተዋል ወይም የSNAP ጥቅማጥቅሞችን ለማስቀጠል በኦገስት 24፣ 2023 ወይም ከዚያ በፊት የዳግም ማረጋገጫ ማመልከቻ እንዲያስገቡ ተጠይቀዋል።

**የታቀደው ስምምነት የሚሰራው ምንድን ነው?** በዚህ ጉዳይ በተሟገቱበት ባለፉት አምስት አመታት ውስጥ DHS የSNAP ፕሮግራሙን ለማሻሻል በርካታ እርምጃዎችን እንደወሰደ ተዋዋይ ወገኖች ይስማማሉ። የበርካታ ሰዎች የSNAP ማመልከቻዎች በሰዐቱ የሚሰናኡ ሲሆን ፣ ብዙ ሰዎች የSNAP ዳግም ማረጋገጫዎቻቸውን በተመለከተ በህጋዊ መንገድ የተጠየቁ ማስታወቂያዎች ይደርሳቸዋል። በስምምነቱ ውስጥ፣ DHS የሚከተሉትን ጨምሮ በብዙ ተጨማሪ እርምጃዎች ተስማምቷል፡-

- DHS በድረገጹ ላይ የፌደራል SNAP ወቅታዊ ሂደት መስፈርቶችን ማክበርን በተመለከተ መረጃን ለማተም ተስማምቷል።
- ለሶስት አመታት ያህል፣ DHS የSNAP ጥቅማጥቅሞችን አስተዳደርን ከሚቆጣጠረው የፌደራል ድርጅት ጋር የደብዳቤ ልውውጥ ማድረግን ጨምሮ፣ ከከሳሾች የህግ ድርጅቶች አንዱ ከሆነው፣ ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህግ እርዳታ ማህበር (ህጋዊ እርዳታ) ጋር ከSNAP ማመልከቻ እና የዳግም ማረጋገጫ ሂደት ጋር የተያያዙ አንዳንድ ሰነዶችን ለማጋራት ተስማምቷል።
- DHS ለተወሰኑ ወጪዎች እና ክፍሉን ለመወከል ለሚያወጡት

ምክንያታዊ የጠበቆች ክፍያዎች ከሳሾች ለፍርድ ቤት ማጽደቂያ ያስገቡትን ማመልከቻ ላለመቃወም ተስማምቷል።

**የመቃወም መብት**

ማንኛውም የክፍል አባል የታቀደው ስምምነት ፍትሃዊ፣ ምክንያታዊ እና በቂ አይደለም ብሎ የመቃወም መብት አለው። ፍርድ ቤቱ በጃንዋሪ 18፣ 2024 10:00 a.m. ላይ የክፍል አባላትን ተቃውሞ ለማመዛዘን በሚከተለው አድራሻ ችሎት አዘጋጅቷል፦

**የU.S ዲስትሪት ፍርድ ቤት የኮሎምቢያ ዲስትሪክት፣ Courtroom 27A**
**333 Constitution Avenue, N.W.**
**Washington, D.C. 20001**

የክፍል አባላት በችሎቱ ላይ በመቅረብ ወይም እስከ ጃንዋሪ 5፣ 2024 ድረስ ለፍርድ ቤት የጽሁፍ መቃወሚያ በማቅረብ ስምምነቱን መቃወም ይችላሉ። በችሎት ላይ ጠበቃ እንዲወክልዎት ካሰቡ፣ ተቃውሞ በጽሁፍ ማቅረብ አለብዎት።